ፓኖራማ ቁጥር 94

# የትዝብር አድማስ

ሐምሌ 28 ቀን 2002 ዓ ም

## <u>በወያኔ ሥርዓት ውስጥ ኢንተልጀንሱን ( ስለላውን ) የሚቆጣጠረው ማን ነው</u> ?

የሀገሪቱን የፖለቲካ ሁኔታና ሂደት በቅርብ ለሚከታተሉ የፖለቲካ ታዛቢዎች፥ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ የሥርዓቱ ዋናው ኃይልና ሥልጣን በዕርግጥ በማን እጅ እንደሆነ ለመረዳት ቢሞክሩም፥ ከትክክለኛው ድምዳሜ ማድረስ ግን የተሳናቸው ይመስላል ። በማንኛው ቀለምና ካባ የመጣ የአምባገነን ሥርዓት አራማጅ ሁሉ፥ ለሥልጣኑ መሠረትና ድልዳል አድርጎ የሚገለገልባቸው መሳሪያዎች አሉት። በሕዝብ የተጠላ በመሆኑ የሕዝብን ድጋፍ አለማግኘቱን በሚገባ ስለሚረዳ ፥ በሥልጣን ለመቆየት የመጨቆኛ መሳሪያዎቹን በግድ ማዘጋጀትና ማጠንከር አለበት ። በማነኛውም ወቅትና ሁኔታ የሕዝብ አመፅ ይነሳብኛል ብሎ ስለሚፈራ ፥ አመፁን ለመከላከል ሲል ለሚወስዳቸው የኃይል ርምጃዎች ሁሉ የሚጠቀምባቸውን የመጨቆያ መሳሪያዎች ከእጁ እንዳያፈተልኩበት የተቻለውን ሁሉ ከማድረግ አይቆጠብም ። ከሕዝብ ቁጣና አመፅ ለመዳን ሲል እርሱ ራሱ ያወጣውንም የራሱን ሕግና ደንብ እንኳ ቢሆን ከመጣስና ከማፍረስ ወደኋላ አይልም ። ዛሬ በኢትዮጵያ የተንሰራፋው በአንድ ብሔር ስም የተደረጀው አምባገነን ቡድንም በአሁኑ ወቅት የሚያደርገው ይህንኑ ነው ። የዛሬይቱን ኢትዮጵያ የሚገዛት <u>ይህ ዘረኛ ሥርዓት የሚከተሉትን የመጨቆኛ</u> <u>መሳሪያዎች</u> <u>ከራሱ ብሔር ብቻ በተወጣጡ አባላት ስር አዋቅሮ ተቆጣጥሯቸዋል።</u>

እነርሱም፡-

1ኛ. በሕዝብ ደኅንነት ስም የተዋቀረው የወያኔ የመረጃና የስለላ ድርጅት ፡-

2ኛ. በጀርመኑ ጌስታፖ አምሳያ የተዋቀረው የፖሊስ ድርጅት፡-

3ኛ. ለመጭቆኛ የተፃፉትን የወያኔን ህግ የሚተረጉሙና የሚፈርዱ ዳኞችና ፥ፍርድ ቤቶች እንዲሁም የተቃዋሚው ክፍል የሚታጎርበት ወኅኒ ቤቶች ፡-

4ኛ. ለምርመራና ለማሰቃያ የተሰናዱ ዘመናዊ መሳሪያዎች፡-

5ኛ. የሕዝብን አመፅ ለመቋቋም ሲባል የሰለጠነ፥ የታጠቀና የተደራጀ ሠራዊትና አፋኝ ቡድን ሲሆን፥ ለዚህም፥ የኣጋዚና የፌዴራል ጦር ድርጅቶች ለምሳሌ የሚጠቀሱ ሆነዋል ።

6ኛ. ፕሮፓጋንዳውን የሚያካሂድበት የመገናኛ ብዙሃንን መቆጣጠርና ሕዝብ እንዳያውቅ ነፃ ጋዜጦችን መከልከል ፥ የንግግር ፥ የመጻፍና የኅሊና ነፃነትን ማፈን፥

7ኛ. በኅብረተሰቡ ውስጥ ተሰግስገው ወሬ የሚቃርሙትን ሰላዮች በብዛት ማሰማራት ናቸው። ሰማኒያ አምስት ሚሊዮን ሕዝብ አፍኖ ለመግዛት በየቦታው ዕልፍ አዕላፍ ሰላይና ጆሮ ጠቢ ቢሰማራ ግን አይደንቅም።

ወያኔዎቹ እነኝህን ሁሉ የመጨቆኛ መሳሪያዎች ያደራጁት ፥ ሕዝቡን ስለማያምኑ፥ ስለሚጠሉና ስለሚፈሩ ብቻ ነው ። ይህ የተጠናከረው የወያኔ የስለላ ድርጅት በኢትዮጵያ ውስጥ ለተነሰራፋው የአምባገነን ሥርዓት ዋልታና ማገር ሆኖ ከማገልገሉም በላይ፥በውስጡ በአንድ በረት ውስጥ የተከማቹ አጋንንትን አቅፏል ። እነርሱም ዛሬ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የተጫኑ መርገሞችን ናቸው። ይህን ግዙፍ የአጋንንት ድርጅት ዛሬ ለማን እንደሚታዘዝና ማንስ እንደሚቆጣጠረው ለይቶ ማወቅ ከማይቻልበት ደረጃ ተደርሷል ። የአምባገነኖቹ የፖለቲካ ተቆጣጣሪዎች ይሁኑ ወይስ ራሳቸው የመረጃው ክፍል መሪዎች ናቸው ይህን ግዙፍ የስለላ ድርጅት የሚቆጣጠሩት ብሎ ለማለት አስቸግሯል ። ይህንን ግዙፍ የኢንተሊጀንስ ድርጅት የፈጠሩት መለስና ጓደኞች መሆናቸው ቢታወቅም ፥ ከስፋቱና ከግዝፈቱ፥ ከውስብስብነቱና በውስጥ ከተሰማሩት ሠራተኞችና ሰላዮች ብዛት የተነሳ ሊቆጣጠሩትና ሊያዝዙት አልቻሉም ። የስለላው መዋቅሮች የተንዛዙ ፥ የተወሳሰቡና የተጠላለፉ በመሆናቸው የትዕዛዝ ሰንሰለቶቹም እንደዚሁ የተዘበራረቁና እርስ በርሳቸው የተምታቱ ናቸው።የኢንተልጀንስ ዘገባ አቀራረብ ተጠያቂነትና ኃላፊነትም ደብዛው ስለሚጠፋ በነመለስ ዜናዊና በመረጃው መስሪያ ቤት ኃላፊዎች መካከል የሚፈጠረው ብዥታና መቁነጥነጥ ከቁጥጥራቸው ውጭ እየሆነባቸው መምጣቱን ውስጠ-አዋቂዎች ይናገራሉ ። መለስ ዜናዊ የራሱን የቅርብ ሰዎች እንኳን ስለማያምን ዓላማው፥ ኢንተሊጀንሱ ለራሱ ብቻ ታዛዥና ታማኝ እንዲሆን ነበር ። ይህ

ታማኝነትና ታዛዥነት ግን ከእጁ እያፈተለከበት በመሄድ ላይ ነው። ወያኔዎቹ ፥ እርስ በርሳቸው ስለሚጠራጠሩና ስለሚጠባበቁ አንዱ ሌላውን በመከታተል ደህንነታቸውን ለመጠበቅ ይፈልጋሉ ። ህይወታቸውን በሙሉ ፥ እርስ በርሳቸው እንደ ጅብ የጎሪጥ እየተያዩ ይኖራሉ።

ይህ ሁሉ ጣጣ የሚመጣው ፥ የዲሞክራሲ ሥርዓት ካለመኖሩ የተነሳ ነው ። የዲሞክራሲ ሥርዓት በሰፈነበት ሀገር፥ ግንኛው ኃይልና ሥልጣን የሚመነጨው ከግለሰቦች ሳይሆን ከሕዝብ በመሆኑ ፥ ሁሉም መንግሥታዊ ተቋማትና ባለሥልጣናት የሚመሰረቱት በህግ ላይ ነው ። <u>የህግ የበላይነት መስፈን የሀገሪቱ ለአላይ ባለሥልጣን ሕዝብ ያፀደቀው ሕገ መንግሥት መሆኑን ያረጋግጣል</u> ። ይህም በመሆኑ ፥ መንግሥትና ሌሎች መንግሥታዊ ተቋማት ሁሉ የህገ መንግሥቱ ተገዥዎች ናቸው ። <u>በመሆኑም ፥ ኃላፊነትና ግዴታቸው፥ ተግባራቸውና ተጠያቂነታቸው ለሀገሪቱ ሕገመንግሥት ስለሚሆን፥የሚያከናውኑት ተገባር ሁሉ አጉራ-ዘለልና ገደብ-የለሽ ሊሆን አይችልም።</u> በአንድ ነፃ ሀገር የኢንተለጀንስ ድርጅት አገልግሎት ጠቃሚነቱ የሚያጠያይቅ ባይሆንም፥ ይህ ዕምነት ግን ዛሬ አምባገነን ሥርዓት በተንሰራፋበት ሀገረችን ቦታ የለው። የኢንተልጀንስ ተቋማትና ጠቃሚነታቸው ለሕዝብና ለሀገር ሳይሆን ፥ለሕዝብ መጨቆኛ፥የአነመለስ ዜናዊን ሥልጣን መጠበቂያ፥ታቃዋሚዎቹን ማጥፊያና ተፃራሪዎችን መጥቂያ መሳሪያ ሆኗል ።

ከሰሃራ በታች ካሉት አፍሪካ ሀገሮች ውስጥ ተወዳደሪ አይገኝለትም የተበለልት ይህ የወያኔ የስለላ መስሪያ ቤት ፥ የቴክኒክ ርዳታና ስልጠና ከእስራኤል፥ ከእንግሊዝ ፥ ከአሜሪካና ከቻይና እንደሚለገስለት የአደባባይ ምሥጢር ከሆነ ቆይቷል ።እነኝህ ሀገሮች ለወያኔ ይህን ርዳታ የሚለግሱለት ሽብርተኝነትን ለመዋጋትና የአካባቢውን ሠላምና መረጋጋት ለመጠበቅ በሚል ሽፋን እንደሆነ ከኢትዮጵያ ሕዝብ የተሰወረ አይደለም ። <u>ስማኒያ አምስት ሚሊዮን በሚሆነው በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ሽብርተኝነትን ለሚያካሄደው ወያኔ ይህንን ርዳታ የሚያደርጉት፥ሽብርተኝነትን ለመከላከል በሚል ሽፋን መሆኑ ፥ እራሳቸውን ለማታለል ካልሆነ በስተቀር የኢትዮጵያን ሕዝብ ሊያታልሉት አይችሉም</u> ። <u>የሀገራችንን ሕዝብ የማሰብ ችሎታ መፈታተናቸው ግን ያስደንቀናል ።</u> ከሩቁ የየሀገራቸው ስትራተጂያዊ ጥቅም አኳያ በተገናዘበ ዲፕሎማሲያዊ ዕይታ ቢያስቡብት ኖሮ፥ ዕፍኝ ከማይሞሉ ወያኔዎች ይልቅ፥ የመላው የኢትዮጵያን ሕዝብ ወዳጅነትና ትብብር ይበልጥባቸው ነበር ። <u>ነገር ግን በመንግሥታት መካከል የሚፈጠረው ሽርክና ፥ ጀርባየን እከከልኝና እኔም ልከክል በሚል ጊዚያዊ ጥቅም ላይ የተመሰረተ በመሆኑ በኢትዮጵያ ሕዝብ አመፅ ወያኔ ሲገረሰስ ፥ የዛሬ ወዳጆቹ ነገ ስልፋቸውን እንሚገለብጡ ስለምናውቅ ብዙም አያሳስበንም ።</u> ለጊዜው ግን

ከአሸባሪው የወያኔ ቡድን ጋር ተሰልፈው የኢትዮጵያን ሕዝብ እንደሚጎዱ ሊያውቁት በተገባ ነበር ።

ዛሬ ይህን የወያኔን ኢንተልጀንስ ድርጅት፥ እኔ ልቆጣጠረው ፥ እኔ ልቆጣጠረው በማለት ሁለት ቡድኖች እንደሚፋተጉበት የውስጥ አዋቂዎች ይናገራሉ ። የወያኔ የፖለቲካ አመራር፥ ማለትም ፥ የመለስ ዜናዊ የፖለቲካው ቡድንና በጠቅላላው የኢንተለጀንሱ አገልግሎት መካከል የመረጃውን አገልግሎት ለመቆጣጠር ፍጥጫው እየከረረ እንዳለ ይነገራል።እንደዚሁም በወታደራዊው ኢንተልጀንስና በሲቪሉ የመረጃ መስሪያ ቤት መካከል የማያቋርጥ የሥልጣን ሹክቻ እንደሚደርግ የቅርብ ተከታታዮች ይገልጹታል። ይህ እንዳለ ሆኖ፥በየመረጃ አገልግሎቶች ውስጥ ብቅ እያሉ የሚወጡት ኃይለኛ ሰዎች፥ለመለስ ዜናዊና ቡድኑ ከፍተኛ የራስ ምታት መሆናቸው አለቀረም ። ሁሉም የመረጃ አገልግሎቶች መሪዎች፥ ነገ ምን እንደሚደርስባቸው ስለሚገነዘቡ ፥ ትኩረታቸው ሀብት በመሰብሰብና በማሸሸ ላይ እንደሆነ የአደባባይ ምሥጢር ሆኗል ። ፖለቲካው ተቋም በራሱ መዋቅር የሚያገኘውን መረጃ ለኢተንለጀንሱ ክፍል አስቀድሞ ሲያሳውቀው ሁሉጊዜ ተገቢውን መልስ የሚሰጠው መረጃውን ከውጭ ኢንተሊጀንስ አጣርቶ እንደሆነም ይነገራል ። ይህም ራሱን የቻለ የግጭትና ያለመተማመን ምክንያት እየሆነ መጥቷል። ታዲያ ዛሬ፥ የወያኔን ኢንተለጀንስ አገልግሎት ማን እንደሚቆጣጠረውና እንደሚያዘዘው በግልጽ አይታወቅም። ለኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ይህ ክስተት ልዩነት የለውም። ለውጥም አያመጣም ። ምክንያቱም ይህን የወያኔን የመረጃ መስሪያ ቤት የሚቆጣጠሩት ፥ ሲቪሎቹም ይሁኑ ወታደሮች ዓላማቸው ሥልጣናቸውን አጠንክረው ሕዝብን እየጨቆኑ ኢትዮጵያን ማፈራረስና መበታተን ስለሆነ ነው ።

ማንም ጨቋኝ አገዛዝ በወታደሩ ብዛትና በስላላ መዋቅሩ መጠናከር ከውድቀቱ አምልጦ አያውቅም። የሕዝብ ትግል ያደባየዋል ። ቢሆንም ግን ከወያኔ ስለላ መዋቅር ራስን ለመከላላከል አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግና እርምጃም መውሰድ ያስፈልጋል ። ርምጃውን ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ ደህና አድርጎ ያውቀዋል።